**Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto**

**ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ**

E-mail: torontofinote@gmail.com

ጃንዋሪ 25 ቀን 2020

ለተከበራችሁ ወድ ኢትዮጵያውያን ወገኖች

በቶሮንቶ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በሀገራችን የሚካሄደውን ህዝባዊ ትግል ለመደገፍና አገራችንን ከአደጋ ለማዳን የየትኛውምየፖለቲካ ድርጀት ደጋፊ ወይምአባል ብንሆንም አለዚያምገለልተኛ ብንሆንም፣ በኢትዮጵያዊነት አቋምና መንፈስ ብቻ ተሰባስበን፤ ድምጽ ለሌለውሕዝባችን ድምጽ ለመሆን፣ እርዳታ ለሚያስፈልገው ወገናችን እርዳታ ለማድረግ፣ በኢትዮጰያ ለሰብአዊ ሙብቶች መከበር፣ አገራችንን ወደ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንድታመራ ለማድረግ፣ ከጎሳና ሃይማኖት ግጭት ሳቢያ የእርስ በእርስ ጦርነትና እልቂት ብሎም ኢትዮጵያን ከጥፋት አደጋ እንዳይከስት ለመታደግ በጋራ ድምጻችንን እንድናስማ ተወያይተን ዓላማና ተግባራችንን ግልጽ አድርገን ‘አገር (ኢትዮጵያን) አድን አስተባባሪ ጊዜያዊ ኮሚቴ’ በሚል መንቀሳቀሳችንና በይበልጥምተወያይተን ቋሚኮሚቴ ለመመስረት መስማማታችን ይታወሳል፡፡

ሆኖምግን ያንን ተግባራዊ ሳናደርግ በርካታጊዜያቶች አለፉ፡፡ አሁን ደግሞአገራችን እጅግ አሳሳቢና አደገኛ ሁናቴ ወስጥ ትገኛለች፡፡ የጎሳና የሃይማኖት ግጭት አደገኛ ወደሆነ አቅጣጫእያመራ ለእርስ በእርስ ጦርነት ከበቂ በላይ ምልክቶች እየታዩ እኛ ዝም ብለን መቀመጥ የለብንምብለን ሰለምናምን፤ የተጀመረውን አገር አድን ኮሚቴ በቶሮንቶን መስርተን ወደ ስራ ውስጥ መግባት እና የምንችለውን ሁሉ ማድረግ መጀመር አለብን በማለት በፌብርዋሪ መጀመሪያ አካባቢ ባሉት ቀናቶች ተገናኝተን ለመወያየት እቅድ ሰለተያዘ፣ በእርስዎ በኩል እንዲዘጋጁበት እያሳሰብን፣ ሃሳብ ካለዎት ወይንምይህን ስራችንን የሚረዳ መንገድ የሚጠቁሙ ቢሆን በደስታ እንቀበላለን፡፡ የመገናኛ ቀኑን እና ቦታውንም ጊዜውሲቃረብ እናስታውቅዎታለን፡፡

አገር አደን ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ